# ***<u>የጠቅላይ ሚኒስትር ባለቤት ወ/ሮ ሀዜብ መስፍን የ150 000 ብር ግብዣ ተደረገላቸው::</u>***

ለቀዳማዊት እመቤት ወ/ሮ አዜብ መስፍን አቀባበል፣ ግብዣና ስጦታ ከ150ሺ.ህ ብር በላይ ወጪ መደረጉ ተገለፀ:: የጠቅላይ ሚንስትሩ ባለቤት ለህዝቡ ጥያቄ አይመለከተኝም፣ የአስፈፃሚ አካል አይደለሁም የመሳሰሉ ምላሾችን መስጠታቸው በስብሰባው አስተባባሪዎችና በነዋሪዎች ላይ ቅሬታን ፈጥሯል::

ቀዳማዊት እመቤት ወ/ሮ አዜብ መስፍን ሰሞኑን በደቡብ ክልል በመዘዋወር የተለያዩ ህዝባዊ ስብሰባዎችን አካሂደዋል:: በሀገር አቀፍ ደረጃ ሴቶችን ከኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተቋቋመውን ብሄራዊ የኤች.አይ.ቪ. ጥምረትን በቦርድ ሰብሳቢነት የሚመሩት ወ/ሮ አዜብ በወልቂጤ ከተማ ባደረጉት ስብሰባ ላይ ከተሰብሳቢዎች ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ሞክረዋል:: አብዛኛው መልሳቸው እኔን አይመለከተኝም፣ አስፈፃሚ አካል አይደለሁም የሚል እንደነበር ከስብሰባው ተካፋዮች ለመረዳት ተችሏል::

ቀዳማዊት እመቤቷ ሴቶችን ከኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ ለመከላከል ኑሯቸውን ማሻሻል፣ የልጆችና የእናቶችን ጤንነት መንከባከብ፣ ሴቶችን ማስተማር የሚሉ ቃላትን ደጋግመው መጠቀማቸውን ያስታወሱት ምንጮቻችን ይህን ለማሟላት ያስፈልጋሉ ያልናቸውን ጥያቄዎች ብንጠይቅም ምላሽ ማገኘት አልቻልንም ብለዋል::

ወልቂጤ የዞኑ መቀመጫ ከተማ ብትሆንም ሆስፒታል፣ ንፁህ የመጠጥ ውሃ፣ ኮሌጅ የለም፣ ሥራአጥነት ተስፋፍቷል፣መሀይምነትና ድህነት ካልተቀረፈ ቫይረሱን መከላከል አይቻልም የሚሉ ሀሳቦችን ብናነሳም አጥጋቢ ምላሽ ሊሰጡን አልቻሉም የሚሉት የስብሰባው ተካፍዮች ወይዘሮዋ ይሄ አይመለከተኝም፣ አስፈፃሚ አካል አይደለሁም የሚሉ ምላሾችን ብቻ ነው ሊሰጡን የቻሉት ይላሉ::

የቀዳማዊት እመቤቷ የጉዞ ዓላማ የሚሊኒየሙን ፀረ-ኤች.አይ.ቪ. ዘመቻ ውይይትን ለመምራት፣ ሴቶች በበሽታው ለይ ያላቸውን ግንዛቤ ለማስፋትና በሽታውን ለመቆጣጠር የሚቻልበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ታስቦ ቢሆንም የጠ/ሚንስትሩ ባለቤት የሚመሩት ቦርድ በዚህ ሁኔታ ምን ያህል ችግሩን ማቃለል እንደሚችል በርግጠኝነት መናገር ይቸግረኛል የሚለው በዞኑ ማስታወቂያና ባህል መምሪያ በህዝብ ግንኙነት በማገልገል ላይ ስሙ እንዲገለፅ ያልፈቀደ የስብሰባው ተሳታፊ ነው::

እንደ ህዝብ ግንኙነት ባለሙያው ገለፃ እስካሁን የትኛውም የፌደራል ባለስልጣን መጥቶ ከተማችንን አላየም፣ የዞኑ መስተዳድርም ችግሮችን ከመፍታት ይልቅ እያወሳሰበ ነው በማለት ይገልፃል:: ነዋሪዎቹም ችግራችን ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ በመምጣት የምንጠጣው ውሃ የማጣት አደጋ ከፊታችን እየጠበቀን ነው፣ ልጆቻችንን ማስተማር ብንፈልግ የግድ ወደ ሌሎች ክልሎች መላክ ይጠበቅብናል ይህም ለከፍተኛ ወጪ እየዳረገን ነው ሲሉ በስልክ ያነጋገርናቸው የስባሰባው ተሳታፊዎች ገልፀውልናል:: እንደ ምንጮቻችን ገለፃ በዚህ ጊዜ የጠ/ሚንስትሩ ባለቤት መምጣት ለጥያቄዎቻችን መልስ ያስገኝልናል ብለን ብንጠብቅም ያሰብነውን ሊነግሩን አልቻሉም ብለዋል::

የሥራ እድል ይፈጥራል ሴቶችን ተጠቃሚ ያደርጋል ተብሎ በዘመቻ መልክ የተጀመረው የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ፤ በግንባት እቃዎች ውድነት እና በውሃ እጥረት ምክንያት በታቀደለት ጊዜ መጠናቀቅ አለመቻሉን የሚገልፁት ነዋሪዎቹ ለግንባታ የሚሆነውን ውሃ ወራቤ ከሚባል ወንዝ በማመላለስ ለመስራት እየተሞከረ ነው:: ዞኑም ለውሃ ማመላለሻ ለተከራየው ቦቴ በወር 35ሺ. ብር ወጪ እያደረገ መሆኑን ነዋሪዎቹ

ይገልፃሉ። በተጨማሪም የተረጋጋ የሥልጣን ጊዜ አለመኖርና የመልካም አስተዳደር እጦት ከተማዋን ለኤድስና ለድህነት ተጋላጭ አድርጓታል ሲሉ ይገልፃሉ።

የከተማው ነዋሪ በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ እያለ ነው ወ/ሮ አዜብ ለስብሰባ የመጡት የሚሉት ምንጮቻችን እርሳቸውን ለመቀበል፣ ለመጋበዝና ሥጦታ ለመስጠት ዞኑ ከ150ሺ ብር በላይ ወጪ አድርጓል። ስብሰባውን ለማድመቅ ለተመረጡ ሴቶች አዲስ ልብስ ለማሰፋት፣ ለቀዳማዊ እመቤቷ ስጦታ ለመግዛት እና ግብዣ ለማድረግ ሲባል ገንዘቡ ወጪ መደረጉን ምንጮቹ ገልፀውልናል። የመንግስት ሰራተኞች ከጠዋቱ 12:30 ጀምሮ በካፊያ እየተመታን አቀባበል እንድናደርግ ተገደናል የሚሉት ግለሰቦች ይህም ሆኖ የከተማችንን ችግር ሰምተውልን በሄዱ በማለት ይናገራሉ።

በጉራጌ ዞን በአጠቃላይ ከ69ሺ በላይ ወላጅ አልባ ህፃናት ያሉ ሲሆን በቅርቡ በማረቆ ወረዳ በተከሰተ ድርቅ በርካታ ህፃናት መጎዳታቸውንና በመመገቢያ ጣቢያ ውስጥ በህክምና ላይ መሆናቸውን የተለያዩ ዘገባዎች ይጠቁማሉ።